## <u>እሾህ በቀለበት ሀገርም አርጅቶ (ተስፋሁን ሞላ)</u>

እሾህ በቀለበት ሀገርም አርጅቶ

የምብርክክ አስኬደው ሰውን ሁሉ ወግቶ።

ነቅሎ የሚያወጣው ወረንጦውም ጠፋ

ሰው ሁሉ ተወግቶ ተኝቶ አንቀላፋ።

እሾሁ ካልጠፋ ጠላት የተከለው

ሀገር ጤና አይገዛም ሁሌ መታመስ ነው።

እባክህ ፈጣሪ እሾህን አጥፋና አብጅለት መንገድ

ሰው ሁሉ ሳይፈራ በሰላም እንዲሄድ።

ህጻን ሽማግሌ ሴት ሳይል ወንድ

ሁሉም በመረጠው በአሰበው ይህድ

አጥሩን ስበርና ስራለት መንገድ።

አንተ የዚያ ብሄር አንተ የዚያ ክልል

ከዚህ ምን አመጣህ እያሉ ሰውን ሁሉ መግደል

አሸባሪ እያሉ ሕዝብን በሃሰት መወንጀል

አስሮ ማንገላታት በእሳት ማቃጠል

የቀን ተሌት  ሥራ ተግባር አድርገውታል

ኢትዮጵያ ሀገራችን አስመሰሏት ሲኦል።

ፖለቲከኞችም ልዩነት አታድርጉ በቋንቋ በብሄር

ሁላችሁ ታገሉ ለአንድ ሕዝብ ለአንድ ሀገር

ወያኔ ተይዞ እጅ እግሩ እንዲታሰር።

አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጋምቤላ፣ ኡጋዴ፣ ሲዳሞና አፋር

ሁሉም በየአለበት ሳይለያይ በቋንቋ በብሄር

መላው ኢትዮጵያዊ አምኖ በአንዲት ሀገር

ድሮ እንደተነሳው ዳር ይዞ እስከ ዳር

አሁን ተሰልፏል አልቅሶ ወያኔን ሊቀብር

ትግሬ ተነጥለህ አደራ ብቻህን እንዳትቀር

በኋላ እንዳትረግምህ የኢትዮጵያ ምድር።

ጥሪው ሲያስተጋባ አንድ የሚያደርግ ሁሉን

ሰላም ለመባባል ለመመስረት ፍቅርን

አንተም ይህን ሰምተህ ተቀላቀል አሁን

በኋላ አታገኝም ኢትዮጵያዊ ነትከን

ወያኔ እንደሆነ ከዶታል ጊዜና ዘመን።

ሁሉም ሲሰባሰብ አምኖ በኢትዮጵያ ነቱ

አንተ ተለይተህ እንዳትቀር በከንቱ

አብረህ ተሰልፈህ ከወያኔ ሙቱ።

ክብሪት ተጭሮ እሳት ሲቀጣጠል

በኋላ አይጠቅምህም ከላይ ከታች ብትል

አሁን አስብበት ነገ ዛሬ ሳትል

ይህን እየሰማህ ጀሮ ዳባ አትበል።

የእጅ አትቀርምና መቀበል ፍዳና ስቃይ

ይህ ከመሆኑ በፊት ይቅርታ ጠይቅ ተሸከመህ ድጋይ

ይዘህ አስረክብ የሰው ደም መጣጬን ይህን ሀገር በዳይ

ኢትዮጵያዊነትከን አሁኑን አስመስክረህ አሳይ

ለትግራይ ወገኔ የማስተላልፈው የለም ከዚህ በላይ።

ከላይ ሆኖ አይቶአል ፈጣሪያችን እግዜር

የሕዝቡን መከራ ስቃይና ችግር።

ክርስቲያን ሁሉ እግዚኦ መሃረነ እያለ ይማለል

እስላምም ተነስቶ አላህ አክብር ይበል

የዲያብሎስ ሰራዊት አጋዚ የሚባል

ሁሉም ተጠራርጎ ወደ ገደል እንዲጣል

በእግዜር ባለመዋል በቅዱስ ሚካኤል

በሰላም አብሳሪው በቅዱስ ገብርኤል።

በዬ አላችሁበት ክርስቲያን፤ እስላም

እግዜርን ለምኑት ለፍቅር ለሰላም

የሰይጣኑ ፈረስ ባሕር እንዲሰጥም።

ኢትዮጵያን ጠብቃት ቸሩ መድኃኔ ዓለም!

ልጆቿን በአንድነት ሰብስባ እንድትኖር ዘለዓለም።

የካቲት፤፲፭ ቀን፡ ፪ሺ፯ ዓ/ም (22/02/2015)